የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፸፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 71
ADDIS ABABA-22nd July, 2003

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ)
ደንብ ........................................ ገጽ ፪ሺ፪፻፴፪

CONTENTS

Regulatios No. 87/2003
Commercial Registration and Licensing Council of Ministers /Amendment/
Regulations ........................................ Page 2232

**ደንብ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፺፭**
**የፌዴራል መንግሥት የንግድ ምዝገባና**
**ፈቃድ ደንብን ማሻሻል የወጣ**
**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፱ አንቀጽ ፵፯ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

REGULATIONS NO.87/2003
REGULATIONS TO AMEND
THE FEDERAL GOVERNMENT COMMERCIAL
REGISTRATION AND LICENCING REGULATION

These Regulations are issued by the Council of Ministers persuant to Article 5 of the Definition of powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47 of the Commercial Registration and Licensing Proclamation No. 67/1997.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Commercial Registration and Licensing council of Ministers /Amendment/ Regulations No.87/2003".

፪· <u>ማሻሻያ</u>

የፌዴራል መንግሥት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፹፱ ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

ሀ)· በደንቡ አንቀጽ ፫ ላይ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል።

"፫· ሚኒስትሩ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ የማመልከቻ የፈቃድና የምስክር ወረቀት ቅጾችን ያዘጋጃል።

፬· በደንቡ ውስጥ "ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ "ለ" ወይም "ሐ" የተመለከተውን አግባብ ያለው ቅጽ በመሙላት" የሚሉት ሀረጎች "ሚኒስቴሩ የሚያዘጋጀውን አግባብ ያለው ቅጽ በመሙላት" በሚሉት ሀረጎች ተተክተዋል።"

ለ) ከደንቡ ጋር ተያይዞ የነበረው ሠንጠረዥ 'ሀ' ከዚህ ማሻሻያ ጋር በተያያዘው አዲስ ሰንጠረዥ ተተክቷል።"

፫· <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

2. *Amendment*

Federal Government commercial registration and licensing council of Ministers regulations NO. 13/1997 is hereby amended as follows.

a. The following new sub-articles (3) and (4) are added to Article 3 of the Regulations.

"3. The Ministry shall prepare application,Licence and certificate forms which will be used for different purposes.

4. In the Regulations the phrase "by completing the appropriate form in the schedule "B" or "C" of these Regulations is replaced by the phrase "by completing the appropriate form prepared by the Ministry."

b. Schedule 'A' which was attached to the regulation is replaced by the new schedule attached herewith."

3. *Effective Date*

Thes Regulations shall enter into force as of the 22nd day of July, 2002.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of July, 2003.

Meles Zenawi
Prime Minister of the Federal
Democratic Republic of Ethiopia

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

